TOTAL
COMMITTED TO BETTER ENERGY

# ቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ.
# የጤና፣ የደህንነት፣ የአካባቢ እና የጥራት ቻርተር

## አንቀጽ 1

ቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. የቶታል ዋና መሥሪያ ቤትን የጤና፣ የደህንነት፣ የአካባቢ እና የጥራት ቻርተርን ያከብራል። ከብሔራዊ ሕጎች እና ደንቦች ጋር በማዛመድ ተግባራዊ ያደርጋል።

## አንቀጽ 2

ቶታል ኢትዮጵያ የደንበኞቹን ፍላጎት ማርካት የሚቻለው በላቀ አገልግሎት ብቻ ሳይሆን፣ እንዲሁም በሰዎች፣ በንብረትና በአካባቢ ላይ የእሳትና ሌሎች አደጋዎችን ሊፈጥሩ የሚችሉ ክስተቶችን በማስወገድም ነው ብሎ ያምናል።

## አንቀጽ 3

የቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. ሥራ አመራር እና ሠራተኞች የሥራ አፈጻጸም ምዘና ለደህንነት፣ ለሰው ልጅ ጤንነት፣ ለአካባቢ ጥበቃ እና ለደንበኞች እርካታ በሚያበረክቱት አስተዋፅኦ እና የኩባንያውን የሥራ መመሪያዎች ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ይሆናል።

## አንቀጽ 4

ቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. ንብረት የሆኑ እና/ወይም ኩባንያው የሚገለገልባቸውን ሥፍራዎች ወይም የኩባንያው ተወካይ ሆነው የሚያገለግሉ በሙሉ በከፍተኛ የንጽሕና ደረጃ እና በሥርዓት የተደራጁ ሆነው የጤና፣ የደህንነት፣ የፀጥታ፣ የአካባቢ ጥበቃ እና የምርት/አገልግሎት ጥራት መስፈርቶችን እንዲያማሉ ይደረጋል።

## አንቀጽ 5

ደህንነት የቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. ዋና እሴት ነው። እንዲሁም ለመንገድ ደህንነት እና ለነዳጅ ምርት ማጓጓዣ፣ አያያዝና ክምችት ቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. ትኩረት ይሰጣል። ስለዚህም የባህሪ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል የደህንነት ሥራ አመራርን በሁሉም ቦታዎችና የሥራ ክፍሎች በመዘርጋት ተከታታይ ፍተሻዎችንና ማስተካከያ እርምጃዎችን ይተገብራል።

## አንቀጽ 6

በሥራችን ሂደት የኃይል እና የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀማችንን ለመቀነስ ጥረት እናደርጋለን። በሥራችን ምክንያት የሚፈጠሩ ተረፈ ምርቶችንና ውዳቂዎችን ለመቀነስ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፣ እንዲሁም በአካባቢ ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ተጽእኖ በመመርመር ተገቢ የሆነ የጉዳት መከላከያ ዘዴ ይቀይሳል።

## አንቀጽ 7

በሁሉም የኩባንያው እንቅስቃሴዎች ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ሁኔታዎች ሁሉ በጥንቃቄ ይፈተሻሉ እንዲሁም ተገቢ የሆኑ የአደጋ መከላከያ እርምጃዎች ይወሰዳሉ። በተለይም ቴክኒካዊ ዘዴዎችን በመጠቀም፣ ሥልጠና በመስጠትና ተግባራዊ ልምምዶችን በማድረግ አደጋን የመከላከል ስራ ይከናወናል። ለተለያዩ አደጋዎች አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ዕቅድ ይነድፋል፣ ውጤቱም በተግባራዊ ልምምዶች ይፈትሻል።

## አንቀጽ 8

ቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. የሥራ አጋሮቹን የሚመርጠው ይህንን የጤና፣ የደህንነት፣ የአካባቢ ጥበቃና የጥራት ፖሊሲ ለመተግበር ያላቸውን አቅምና ፍላጎት በመገምገም ይሆናል።

## አንቀጽ 9

ቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. በሚሠራቸው እና በሚያሠራቸው ሥራዎች በሙሉ ጥብቅ የሆነ የጤንነት፣ የሥራ ላይ ደህንነት፣ የፀጥታ፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ የጥራት እና የማሕበራዊ መመሪያዎች መተግበራቸውን ይከታተላል፣ እንዲሁም መደበኛ ግምገማ ያከናውናል። አዳዲስ ግንባታዎች ወይም ምርቶች አደጋዎችን ሊፈጥሩ ከሚችሉ ክስተቶች ተጠብቀው እንዲተገበሩ ይቆጣጠራል።

## አንቀጽ 10

ቶታል ኢትዮጵያ ከተሰማራበት የሥራ መስክ አኳያ በሚንቀሳቀስባቸው አካባቢዎች ላለው ማኅበረሰብ ተከታታይ የሆነ ዕድገት እንዲኖር አስተዋፅኦ ያደርጋል። በደህንነት እና ሰብአዊ መብቶች ዙሪያ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረቱ መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ ደህንነቱ ተጠብቆ ዋስትና ለመስጠት በሚያስችል መልኩ ተግባሩን ያከናውናል።

# Total Ethiopia S.C.
# Health, Safety, Environment and Quality Charter

## Article 1

Total Ethiopia S.C. respects and it is committed to implement the TOTAL Group's HSEQ Charter in amalgamation of local laws and regulations.

## Article 2

Total Ethiopia S.C. believes that the best long term customer satisfaction is achieved and their loyalty is improved not only through its customer service excellence but also by preventing work related accidents and security events that may cause bodily injury or occupational illness, property or environment damage and loss of business.

## Article 3

The managements and employees of Total Ethiopia S.C. are evaluated on the basis of their contribution to risk prevention and exemplary behaviour towards safety, health, environmental protection and customer satisfaction and with respect to the company's procedures.

## Article 4

All sites and activities owned and/or operated by Total Ethiopia S.C. or its representatives must always be found in compliance with all Health, Safety, Security, Environment and Quality requirements and regulations.

## Article 5

Safety is Total Ethiopia's core value. Furthermore, it gives focus to Road Safety, transportation and storage of petroleum products. Thus, it implements, a Safety Management System with continuous improvement, in all its areas and activities, so as to result in behavioural changes through regular risk assessment, development of control measures and management review of the system.

## Article 6

In our operation, we strive to reduce our energy and natural resources consumption, production of wastes and their possible impact on the environment is continuously assessed and pollution prevention methods are implemented.

## Article 7

In all the activities of Total Ethiopia S.C. systematic analysis of risks are being conducted and preventive actions taken mainly through technical intervention, training, refresher courses. Emergency response plan is established to meet different type of incidents and exercised through regular drills.

## Article 8

Total Ethiopia S.C. favors in the selection of industrial and business partners their ability and willingness to apply policies similar to its own concerning Health, Safety, Security, Environment and Quality.

## Article 9

Total Ethiopia S.C. implements, for all of its operations, appropriate management policies regarding safety, security, health, the environment, quality, societal commitment and a periodic risk assessment of relevant policies. Any development of a project or launch of a product is undertaken upon full lifecycle risk assessment.

## Article 10

Total Ethiopia S.C. is engaged in line with its core business to contribute for sustainable development of neighbouring community with a focus on human, economic and social issues. It conducts its operations in such a way as to responsibly ensure security, in compliance with the Voluntary Principles on Security and Human Rights

Rev. 06 January 2019

**ቲቦ ለሲዩወር**
ዋና ስራ አስኪያጅ

**Thibault LESUEUR**
Managing Director